**ARCHIVED DOCUMENT.** As of December 13, 2022, this document is no longer in force.

# ለአራስ ሕፃናት እና ለታዳጊ ሕፃናት (ESIT) አገልግሎቶች በአካል ወደሚሰጠው ቅድመ ድጋፍ ለሚሸጋገሩ ቤተሰቦች የሚሆን መመሪያ



የ ESIT ፕሮግራም ቤተሰብዎ ሰላም እና ደህና እንዲሆኑ ይፈልጋል። እርስዎን ለማየት የሚመጡ አገልግሎት ሰጪዎች ከመንግስት እና ከኤጀንሲዎቻቸው የሚመጡ መመሪያዎችን ይከተላሉ።

## በአካል ወደሚሰጡ አገልግሎቶች ምሸጋገር አለብን?

የልጅዎ እና የቤተሰብዎ ፍላጎቶች ከሌላ ከማንኛውም ሰው እንደሚበልጥ ያውቃሉ፣ እንዲሁም በአካል ወደሚሰጡ አገልግሎቶች ለመሸጋገር ትክክለኛውን ሰዓት መምረጥ ይችላሉ። የቤተሰብዎ ሃብቶች አስተባባሪ እና ሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎችዎ ስለርስዎ ምርጫዎች ለመወያየት ይገኛሉ።

## የኔ ምርጫዎች ምንድን ናቸው?

ቤተሰቦች የተለያዩ የአገልግሎት አሰጣጥ ምርጫዎች አላቸው። ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን፡

- በቴል ልምምድ አገልግሎቶች ሊቀጥሉ ይችላሉ
- አቅራቢ ወደ ቤትዎ እንዲመጣ መምረጥ ይችላሉ
- እንደ መናፈሻ ወይም ጓሮዎ ባሉ ከቤት ወጣ ባሉ ቦታዎች ከአቅራቢዎች ጋር ለመገናኘት ሊመርጡ ይችላሉ
- ወይም ማናቸውም የነዚህ ነገሮች ጥምረት

## አገልግሎቱ በአካል በሚሰጠበት ጊዜ የፊት ጭንብል(ማስክ) ማድረግ ያለበት ማን ነው?

አቅራቢዎች በቤትዎ ውስጥ ማስክ ያደርጋሉ። በቤት ውስጥ ከመጎብኘትዎ በፊት ፣ ከአቅራቢዎ ጋር አቅራቢው ማስኩን ሲያደርግ ለልጅዎ ምን እንደሚመስል ለማሳየት በመጀመሪያ በቪዲዮ እንዲደዋወሉ ማድረግ ሊያስፈልግዎ ይችላል። ማስክን ማድረግ ሁሉንም ሰው ደህንነት እንደሚጠብቅ ያብራሩላቸው። በአካል የሚሰጠውን አገልግሎቶች የሚወስደው ልጅዎ ማስክ ማድረግ አይጠበቅበትም። ሆኖም ግን ፣ እርስዎ እና ሌሎች ከ አምስት እድሜ በላይ የሆኑ በቤትዎ ውስጥ የሚገኙ ልጆች ግን እንዲያደርጉ ይመከራል።

## አቅራቢዬ ወደ ቤታችን ሲመጣ ፣ ክፍሎቻችን እንደበፊቱ ተመሳሳይ ይሆናሉ?

በአካል ወደ ሚሰጡ አገልግሎቶች ለመሸጋገር ከወሰኑ ፣ አቅራቢዎ የኤጀንሲውን የደህንነት መስፈርቶች ደጋግመው ይመለከታሉ እንዲሁም ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ ይገልጻሉ። እነዚህ መስፈርቶች የመጀመሪያ ጉብኝቶች የተለዩ መስለው እንዲታዩ ሊያደርጋቸው ይችላሉ ፣ ነገር ግን ለእርስዎ ደህንነት ሲባል እዚያ ይገኛሉ። ምንም ያህል የርስዎ አገግሎት ሰጪ አገልግሎቶችን በአካል የሚሰጥ ቢሆንም ፣ ነገሮች ልክ ከወረርሽኑ በፊት እንደነበሩት ላይሆኑ ይችላሉ። በሚጎበኙባቸው ወቅቶች እርስዎ እና ልጆችዎን ምቾት ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

## ተጨማሪ ጥያቄዎች አልዎት?

የልጅዎ የልማት ግቦችን ለማሳካት በምንሰራበት ጊዜ የቤተሰብዎን ደህንነት የሚጠብቁ አማራጮችን ለማግኘት ቁርጠኛ ነን። ምንም አይነት ጥያቄ ካልዎት ፣ አባክዎን የአገልግሎት አቅራቢዎን ወይም የቤተሰብ ሃብቶች አስተባባሪዎን ይጠይቁ።

---

የዚህን ሰነድ ግልባጮች በአማራጭ ቅርፀት ወይም ቋንቋ ከፈለጉ፣ እባክዎ *DCYF Constituent Relations (DCYF አካል ግንኙነቶች) (1-800-723-4831 | 360-902-8060፣* ***ConstRelations@dcyf.wa.gov****)* ያግኙ።

DCYF PUBLICATION FS_0059 AM (04-2021) Amharic

Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

ARCHIVED